## የረቡዕ ጥር 17 1998ዓም( የጃነዋሪ 25 2005)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## ኢትዮጵያና ጀግኖቿ

እንደ ማነኛውም የዓለም ሀገሮች፥ ኢትዮጵያ ሀገራችንም በታሪኳ ስመ-ጥር ጀግኖችና አረበኞች ነበሯት አሁንም አሏት ወደፊትም ይፈጠራሉ። ይኸማ ባይኖር ኖሮ፥ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ዜጎቿም እንደ ሕዝብ ለአያሌ ዘመናት ህልውናቸውንና ነፃነታቸውን፥ ባኅላቸውንና ማንነታቸውን በመጠበቅ በአንድ ላይ መኖር ባልቻሉም ነበር። ለጀግኖቿና ለአርበኞቿ ክብርና ምስጋና ይድረሳቸው እንጅ፥ በእነርሱ መሥዋዕትነት እስከአሁን አለች። የኢትዮጵያ ማህፀን ጀግና መውለድን እስካላቆመ ድረስም ወደፊትም ቢሆን፥ በጀግኖቿና በአርበኞቿ መስዋዕታዊ ተጋድሎ በነፃነቷ እንደምትኖር መጠራጠር አይቻልም። ጅግኖቿና አርበኞቿ፥ ማነኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ለሚወደው ሁሉ፥ ፍቅሩን የሚገልጽበት የመጨረሻ ስጦታ፥ ህይወቱን መስጠት ነው የሚለውን ወርቃማ ህግ በማክበር ተሰውተዋል እንጅ፥ ከድል በኋላ ለሚገኘው ሹመትና ሽልማት፥ ሥልጣንና ማዕረግ፥ ወይም ለከንቱ ውዳሴና ለቁሳቁሳዊ ጥቅማ ጥቅም አልነበርም። የእነርሱ የመጨረሻ ደስታና ክብር የነበረው፥ ሀገራቸውን ከጠላት ወረራና ጥቃት ተከላክሎ ሕዝባቸው በነፃነትና በኩራት መኖሩን ማየትና ማረጋገጥ ነበር። ለሰው ልጅ፥ ከዚህስ የበለጠ የመንፈስ ርካታና ደስታ ምን ሊኖር ይችላል?

የስድሳ ስድቱ ዐብዮታዊ ትውልድም ለሀገሩ ክብርና ለወገኑ ፍቅር ሲል አይከፍሉ መከራና ስቃይ፥ እስራትና ሰቆቃ፥ ግድያና ስደት ሊደርስበት የበቃው፥ ከጀግኖች ወላጆች የወረሰውን ወርቃማ ህግና ቃልኪዳን በመጠበቅ ነበር። ያ ጀግና ትውልድ ለሀገሩና ለሕዝቡ የገባውን ቃልኪዳን በመጠበቅ የተሰዋው፥ በአንድ ብሔራዊ ዓርማና ረዕይ ስር በመሰባሰብ ነበር። ይህም በመሆኑ፥ ሁሉም የትግሉ ተሳታፊ፥ ኢትዮጵያዊ እሴቱና ብሔራዊ ፍቅሩን በአርዓያነት ለተተኪው ትውልድ ማጠየቂያና መሠረት እንዲሆነው አስመስክሮ አለፏል። ለዚያ ጀግና ሰማዕት ትውልድ፥ የትግሉ አልፋና ኦሜጋው መነሻና መድረሻው፥ ሂደቱና የመጨረሻ ግቡ ያው የኢትዮጵያ ሀገሩንና የወገኑን ብሔራዊ ጥቅም ማስከበርና መጠበቅ ነበር። በብሔርና በጎጥ፥ በሃይማኖትና በዘር፥ ወይም በወያኔ ቋንቋ፥ በክልልና በአውራጃ የተደየነ አልነበረም። ያ ጀግና ትውልድ፥ እንደ ጥንት እንደ ጧቱ፥ ከምሥራቅ እስከ ምዕራም ከደቡብ እስከ ሰሜን በአንድ ዓላማና ግብ በመነሳሳቱ፥ ባጭር ጊዜ ውስጥ ተዓምር ሰርቶ ሀገራዊና ታሪካዊ መስዋዕት ለመክፈል ቻለ።

አይበገሬነቱንም በደሙ አስመሰከረ። የገባውን ቃልኪዳን በሕይወቱ አከበረ አስከበረ። ጀግንነቱንም በሚያኮራ ድሪጊት ገለፀ። አርበኝነቱንም በክብር ደሙ እየፃፈ በአኩሪ ታሪኩ እያስመዘገበ ለሚቀጥለው ትውልድ የሚጠቅምና የሚያኮራ የታሪክ ምዕራፍ ጽፎ አለፈ። እየኖሩ መሞትን ብቻ ሳይሆን፥ እየሞቱ መኖርንም ጭምር እያሳየ ክንዱን ተንተራሰ።   የክብር ሞቱን ተጎናፀፈ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ፥ በረዥም የነፃነት ታሪኳ ሂደት፥ ዕልፍ አዕላፍ ጀግና እየተሰዋላት አዕላፍም እየተተካለት ሲወርድ ሲዋረድ እዚህ ደርሷል። በአንድ ትውልድና በሀገር መካከል ሊኖር የሚገባው ቃል ኪዳንና ትስስር፥ በስጠኝና ልስጥህ፥ ጀርባየን እከክልኝና እኔም ልከክል በሚል የገበያና የነጋዴ ስምምነት ላይ በተመሠረተ ውል  ሳይሆን፥ አንድ ዜጋ፥ የዚያ ሀገር ዜጋ በመሆኑ ብቻ በአላፊ ጠፊና በከንቱ ውዳሴ ላይ ባልተገነባ የዜግነት ግዴታና ኃላፊነት፥ ተግባርና ተልዕኮ ላይ የታነፀ ነው። በዚህ ብሔራዊ ፍቅርና ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ ትግል፥ እስከ መጨረሻው ፀንቶ በመቆየት፥ ትግሉ ግቡን እስኪመታ ድረስ፥ በቆመበት ዓላማ ሳይደራደር፥ በሚያጋጥመው መከራና ስቃይ ሳይበገር፥ በሚደርስበት የአክልም ሆነ የሥነ አዕምሮ ጥቃት ፍንክች ሳይል፥ እየተዋደቀ ፥ እየታዘበ፥ የመጨረሻ ግንዱን እየተንተራሰ ያልፋል። በእርሱም ፈንታ ሌላ ጀግና እየተተካ፥ የትግሉን ነዲድ እያቀጣጠለ ይቀጥላል። እስከ መጨረሻው የድል ቀን ድረስ! ይህ ደግሞ፥ የኢትዮጵያዊነቱ ዓብነት፥ የዜግነቱ መስተጋብር፥ የማንነቱ መታወቂያ፥ የትውልዱ መለያ፥ ነው። የሚጠበቅበትን ከመፈፀም በቀር፥ ከሀገሩና ከወገኑ መካካሻም ሆነ ክፍያ፥ መደጉሚያም ይሁን ጉርሻ፥ ሙገሳም ሆነ  ውዳሴን አይጠብቅም።  በዚህ ሥነ አዕምሮ ተሸብበው የነበሩት ግን ብዙ ምዕራፍ ሳይጓዙ መና ሆነው ቀርተዋል።

ቃልኪዳንን እስከ መጨረሻው እየጠበቁ፥ በመርኃ-ግብር እየተጀቡ፥ በትግል ሂደት የጀግና ክንዳቸውን ከተንተራሱት ግንበር ቀደም የሀገሪቱ ብርቅየ ልጆች መካከል፥ በታህሣሥ 20 ቀን  1998 ዓም  ከጧቱ 4 ስዓት  ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው፥  አቶ ሳሙኤል  ዓለማየሁ ነበር።  ለአለፉት ሠላሳ  አራት የትግል ዓመታት ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ  ፓርቲ  ውስጥ ፥ አመራር በመስጠት፥ ታግሎ በማታገል፥  ተምሮ በማስተማር፥ አውቆ በማሳወቅ፥ ታዝቦ በመምከር፥ ተካፍሎ በመብላት፥ ስቆ በማሳቅ፥ ተፅናንቶ በማፅናናት፥ በቀውጢ ስዓት ተረጋግቶ በማረጋጋት፥ ሰርቶ በማሰራት፥ ልዩ ባኅርይና ስጦታ የነበረው ሳሙኤል አለማየሁ፥ ከደርግ የውኅኒ ቤት ስቃይ እስከ የበረሃ ትግል ድረስ የገባውን ቃል ኪዳን በመጠበቅ በዓላማው ፀንቶ ለሀገሩና ለሕዝቡ ታግሏል። ይህን ሲያደርግም ፥ ደከመኝ ልረፍ፥ ታከተኝ ለተወው፥ ሰለቸኝ ልርሳው፥ ዕራበኝ ጠማኝ ሳይል በፅናት በመቆየት እስከ መጨረሸው እስትንፋሱ ማንነቱን ያስመሰከረ ኢትዮጵያዊ ጀግና ፥ የጀግኖች ጀግና ነበር። የትግል ታሪኩን ያቆራኘውም ከእርሱ በፊት በግንባር ቀደም ከተሰውት፥ ዐብዮታውያን ጓዶቹ እንደነ ተስፋይ ደበሳይ፥ ተካልኝ ወለደ አማኑዔል፥ዮሴፍ አዳነ፥ እንጂኔር ዑስማን፥ማርቆስ ሀጎስ፥ ሻምበል አምሀ፥ክፍሉ ከበደና ዮሀንስ ብርሃኔ፥ ፀሎተ ህስቅያስና ብንያም አዳነ፥ መሀመድ ማህፉዝ፥ስንቶቹ ሌሎቹም፥እነ

*ጋይምና አምበርብር÷ከሊፋና ትርሲት÷ፅጌ÷ መስከረምና ጃብር ዕልፍ ሰማዕታት ጋር ስለነበር የተመኘውን የጀግና ሞት አግኝቶ ግንዱን ተንተርሿል፡፡ ሳሙኤል ዓለማየሁ የዛሬ ሠላሳ አራት ዓመት ከትግል ጓዶቹ ጋር ለሀገሩና ለሕዝቡ ቃል የገባው÷ ለኢትዮጵያ የነበረውን ሀገራዊ ራዕይ ዕውን ለማድረግ ነበር፡፡ ሳሙኤል ዓለማየሁና ሌሎች ሰማዕታት ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የነበራቸው ብሔራዊ ራዕይና ዓላማ ምን ነበር? ራዕያቸው÷ ዓላማቸው÷ ዕምነታቸውና ተስፋቸው፡-*

- *የዜጎቿ ዕኩልነትና አንድነት÷ ነፃነትና ልዕልና የተከበረባትን ሀገር መገንባት÷*
- *ከድህነት÷ ከበሽታ ከማይምነትና ከኋላ ቀርነት የተላቀቀች ሀገር ማየት÷*
- *የብሔር-ብሔረሰቦቿ ባኅል÷ ዕምነት÷ ቋንቋና መስተጋብር እንዲበለፅግ እንዲስፋፉና እንዲፋፉ ማድረግ÷*
- *የግዛት አንድነቷ የተከበረ÷ የበለፀገችና የተፈራች÷ ብሔራዊ ልዕልናዋ የታፈረ÷ ተራማጅና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ ነበር፡፡*

*ይህ ታላቅ ብሔራዊ ዓላማና ራዕይ ደግሞ ያለ ትግልና መሥዋዕት እንደማይገኝ÷ እነኛ ብሔራዊ ጀግኖችና አርበኞች÷ ሳሙኤልና ሌሎች ስማዕታት በሚገባ ተረድተውት ነበር፡፡ ለዚህም ነበር አይከፍሉ መስዋዕት እየከፈሉ ÷ለሕዝባቸው የገቡትን ቃል ኪዳን በመጠበቅ ክንዳቸውን እየተንተራሱ ያለፉት፡፡ ክንዳቸውን እሰከ ተንተራሱበት ወቅት ድረስ ግን በሀገራቸው ብሔራዊ ጥቅም ላይ አልተደራደሩም፡፡ የኢትዮጵያን ብሔራዊ አጀንዳ በብሔርና በጎጥ÷ በዘርና በቋንቋ ዳካ አለወሱትም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ስለነበሩ በኢትዮጵያዊነታቸው ኮርተው ተሰውተዋል፡፡ ሳሙኤልንና ጓዶቹን÷ ጓዶቻችንን፤ ይምናከብራቸው÷ የምንወዳቸውና ይምናመሰግናቸውም÷ የትግላችን አካሎች አምሳሎች በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን÷ አኩሪ ታሪካቸው ለተተኪው ትውልድ ብሔራዊ አርዓያና ተምሰሌት በመሆኑም ጭምር ነው፡፡ የነርሱ ዓላማና ራዕይ ዕውን እስከሚሆን ድርስ ትግላችን አናቆምም÷ ትጥቃችንንም አንፈታም በማለት÷ በሳሙኤል ዓለማየሁ መካነ-መቃብር ላይ ጓዶቹ ቃለ-ማሃላቸውን እንደገና ያደሱትም÷ በዚህ መተከላዊ ዕምነትና መሠረታዊ ዓላማ ነበር፡፡*

*በየትኛውም ዘመንና ትውልድ የነበሩት የኢትዮጵያ ጀግኖችና አርበኞች ለሀገራቸው ነፃነትና ክብር ሲሉ ቢንገላቱም ቢሰቃዩም÷ በመጨረሻው ህልፈታቸው ግን÷ ሀገራቸውን እያዘኑላት ተሰው እንጅ÷ አላዘኑባትም፡፡*
*ያ የጀግኖቿና የአርበኞቿ ህዘኔታ እንዳለ ሆኖ ግን÷ አንድ የማይታበል ሀቅ መኖሩ ሊዘነጋ የሚገባ አይመስለንም፡፡ይኸውም÷ ኢትዮጵያ ሀገራችን*

የሚሰውኗትን አርበኞች ልጆቿንና የሚያርዳትን ጠላቷን በሚገባ ታውቃለች ብለን ለመናገር አለመቻላችን ነው:: ለዚህም ይመስለናል፥ " አንች ተላላ ፥ የሞተለሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ" የምትባለው:: ይህ ሀቅ እንዳለ ሆኖ፥ የኢትዮጵያ አርበኞችና ጀግኖች ሰማዕታት ሕይወታቸውን የሰጡላት፥ ውለታ ለመጠበቅ ሳይሆን፥ ሀገራቸው በነፃነትና በብልፅግና፥ በሰላምና በዕድገት፥ ዜጎቿም፥ በዕኩልነትና በአንድነት ተባብረው እንዲኖሩ ነው:: የሳሙኤል ዓለማየሁና የሰማዕታት ጓዶቻችን ዓላማና ራዕይም ይህ ብቻ ነበር:: ታዲያ ሁሉንም ስንሳናበታቸው፥ ይህንን የነርሱን ዓላማና ራዕይ ዕውን ለማድረግ እንዲቻል ትግላችንን በመቀጠል ብቻ ይሆናል:: ዛሬ ተፋፍሞያለው ፀረ ወያኔ ትግል፥ያለመስዋዕትነት ወደ ድል እንደማይጓዝ ግልፅ ነው:: በትግል እየተሰው ያሉትን በአርዓያነት እንከተላለን እንጅ፥አለቁ ተጨረሱ ብለን ደረት አንደቃም:: የኢትዮጵያ ሀገራችን የረዥም ጊዜ ታሪክ የሚያስረዳው ነገር ቢኖር፥ጀግኖች እያለፉ ጀግኖች የሚተኩ መሆናቸውን ስለሆነ፣ ጀግናው ሳሙኤል ዓለማየሁና ሌሎቹም ሞት አይፈሬ የኢትዮጵያ ልጆችያለፉት ፥ ብዙ ቆራጥ ጀግኖችን አፍርተውና ተክተው መሆኑን ወዳጅም ሆነ ጠላት የሚያውቀው ነው::

የጀግና ሰማዕት እናቶች ይኩሩ፥ ይበራከቱ!!
በትግል መሞት ህይወት፥ ዳግም ትንሳዔ ልደት!!

ጀግና አልፎ ጀግና ሲተካ፥
የጀግኖች ፈለግ መች አጣ ዱካ፥
አርበኛ ወድቆ ሲሰዋ፥
የትግሉ ጎራ መች ሆነ ዳዋ፥
ያስተናግደዋል ትግሉን እንዳመሉ
ያቀናብረዋል ስልቱን እንዳመሉ፥
ያገባድደዋል፥ <u>ነገ ይዘገዋል</u> ትግሉን እንዳመሉ
ዛሬ
የት ሄደ ቢሏችሁ ግን፥ <u>ከፍቶት</u> ሄደ በሉ::

ኢትዮጵያ ሀገራችን በነፃነቷ
ለዘለዓለም ትኖራለች!!